# የተሃድሶ አይነቶችና ጥያቄዎቻቸው

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን!

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ እኛ ኦርቶዶክሳዊያን ክርስቲያኖች ከግርግር ይልቅ በውውይት በዳበረ እና ጥናታዊ በሆነ መልኩ ያሉንን መልካም ጎኖችና ደካማ ጎኖች በመለየት ቤተ ክርስቲያንን ከመናፍቃንና ከመከፋፈል ለመጠበቅ እንድንችል ፍንጭ መስጠት ነው። ጸሐፊው በእውነታዎች /ፋክትስ/ ላይ ተመርኩዞ ይጽፋል። ስለተሃድሶ ማንነትና ምንነት ስለሚፈልጉት ነገር ስለሚያቀርቧቸው ክሶች ምነነት በተከታታይ ጽሑፉን ያቀርባል። ቤተ ክርስቲያን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ማድረግ አለባት ተብሎ የሚታሰበውንም ነገር ይዳሰሳል። ለጸሓፊው አስተያየት ለመስጠት በ(christtewahedo@gmail.com) ይጻፉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈቻቸው ጊዚያት ሁሉ በእግዚአብአብሔር እየታመነች እስከ ዛሬ ደርሳለች። ቤተ ክርስቲያን ለአንዳንዶች ባህላዊ ብትመስላቸውም ፍጹም መንፈሳዊ ነች ለአንዳንዶችም ድርሰታዊ ብትመስላቸውም ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነች። አስተምህሮዋ ክርስቶስ ርእስዋና ምህዋርዋም እግዚአብሄርን ማመን በእርሱ መታመን እርሱን መውደድና መታዘዝ ነው። በአንጻሩ ቤተ ክርስቲያን ባህላዊ የምትመስለው ሰው ቢኖር የክርስትናን እምነት ለኢትዮጵያዊው ባህል እንዲሆን ስላደረገች እንጂ እርስዋ ባህላዊ ስለሆነች አይደለም። የክርስቶስ ከጽንሰቱ እስከ እርገቱ አስታውሳ የምታከበረው ባህላዊ ስለሆነች ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነች ነው። ለእግዚአብሔር መታዘዝን የምታስተጋባውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነች እንጂ ባህላዊ ስለሆነች አይደለም።

በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አዛገቶ ስለማይታወቅ የሚፈራ የሚታፈር የሚሰማ የሚከበር በመጥፋቱ ሁሉም እኔ ትክክል ነኝ በሚል ፈሊጥ የየራሱን አመለካከት ትኩረት በመስጠት ክርር ያለ ፉክክርና ዘመቻ እናያለን። ከማህበራቱ እስከ ግለሰቦች ከምእመናን እስከ ፓትርያርክ ያሉ ሰዎች በአንጻሩና የእግዚአብሔር ድምጽ በሆነው በሲኖዶስ ከመታዘዝ ይልቅ የራሳቸውን ወይም ተሰፋ የጣሉባቸውን ሰዎች ሃሳብ መደገፍንና አጀንዳቸውን ማስፈጸም ይሯሯጣሉ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተንሰራፋው የመልካም አስተዳደር እጦት በአንድ በኩል ክርስቲያኖችንና እግዚአብሔርን ሲያሳዝን በቡድን ሆነው ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ ታስተምር የሚሉ አካላት ደግሞ በራሳቸው ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ፈተናዎች ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ቤት እንደመሆንዋ ማንም ሰው ባመጣው ሃሳብና መመሪያ ሳይሆን ራስዋ በሆነው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ብቻ የህዝቡን አኗኗር ከግምት ውስጥ በማስገባት መመራት ይገባታል እንጂ እንዲሁ መሪ እንዳጣ ጀልባ ወዲያና ወዲህ ማለት አይገባትም። በዛሬው እለት ስለተሓድሶዎች አስተሳሰብ እና የእነርሱ ተከላካይ ስለሆነው ማህበረ ቅዱሳን በጥቂቱ ለማለት እፈልጋለሁ።

በአሁኑ ወቅት ማንም ሰው ሊያስተውለው እንደሚችል በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሁለት የሚጋጩና እርስ በእርሳቸው መጠፋፋት የሚፈልጉ አካላትን እናገኛለን። አካላት ስንልም ሃሳቦች ናቸው። ሃሳቦች ግን ሰዎችን ይዘዋል። ሁለቱ አካላት በእየራሳቸው ለአንድ ዓላማ ይኸውም ለቤተ ክርስቲያን ለመጥቀም እንደሚሰሩ ይናገራሉ።

**ማህበረ ቅዱሳንና ማህበረ ቅዱሳናዊ አስተሳሰብ**

ማህበረ ቅዱሳናዊ አስተሳሰብ የምለው ቤተ ክርስቲያን እንከን የለሽ በመሆንዋ ምንም አይነት ትችት ማቅረብ የለብንም የሚለውን እና አብዛኛው የማህበሩ አባላት እንዲሁም ብዙ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎችም የሚጋሩት ነው። ይህ ሃሳብ በመሰረተ ሃሳብነት ማነኛውም ኦርቶዶክሳዊ ሊደግፈውና ሊጋራው የሚገባው ነው። የራስን ቤት ይልቁንም መከራና ዘከራ ያሳደገችንን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ናት እያሉ በእየ ሜዳው ስሟን ማጥፋት ክብሯን ማጉደፍ የማይገባ ስራ መሆኑ እሙን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ምእመናኑ ወደ ኑፋቄ የሚነጠቁበትን እና በሃይማኖት ያሉትም ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የማይቀርቡበትን ምክንያት አጥንቶ እነዚህ እንዲህ ይደረግ ይህ ይስተካከል ማለት አግባብ ነው።

ማህበረ ቅዱሳን በእየ ዜናው መውጣት ከጀመረ አለፈ ከረመ እንዳንዶች አይንህን ላፈረ አይነት ጽሁፍ ሲጽፉበት አንዳንዶች ደግሞ እርሱ ከሌለ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አትኖርም ብለው ክርር ያለ ክርክር ያደርጋሉ። ታዲያ ሁለቱም ትክክል ሊሆኑ ስለማይችሉ ትክክለኛው የቱ ይሆን ማለቱ አስፈላጊ ነው። የዚህ ጽሁፍ ጸሓፊ ማህበሩን በሚገባ የሚያውቅ ድክመቶቹንም የማያስተባብል ስለሆነ የማህበሩን በጎ ጎኖችን ሙሉ በሙሉ ዘርዝሮ መጨረስ ባይችልም ዋና ዋና በጎ ጎኖችንና ድክመቶቹን ይጽፋል። የጽሁፉም አላማ ሰዎች ጥሩውንና መጥፎውን ለይተው ከመልካሙ ጋር እንዲተባበሩ ከመጥፎው ደግሞ እንዲርቁ ነው።

ማህበረ ቅዱሳን ከሚደነቅባቸው ጥሩ ጎኖች መካከል

1. የተማረው ኢትዮጵያዊ/ኦርቶዶክሳዊ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዝና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርብ በርትቶ መስራቱ
2. ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ የአባቶቹን ትውፊት ተከትሎ የቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግል ማበረታታቱ
3. ለቤተ ክርስቲያን አካላት ለገዳማትና ለአድባራት ልዩ ትኩረት በመስጠት እርዳታዎችን ማድረጉ
4. ቤተ ክርስቲያን በምትፈልጋቸው ማናቸውም የሞያ አይነቶች አባላቱን በማሳተፍ በነጻ አገልግሎት ማበርከቱ
5. ቤተ ክርስቲያን ላይ ደባ የሚጥሉትንና እርስዋን ለማጥፋት የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ በአይነ ቁራኛ በመከታተለ ለሚመለከተው አካል ማስረዳቱ
6. ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ አስተዳደር እንዲኖራት ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ለልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አካላት ማበርከቱ
7. አባላቱ በሚችሉት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሳተፉ መገፋፋቱ። ከሰባኪነት እስከ ገንዘብ እርዳታ እንዲያደርጉ ስልጠናና ምክር መስጠቱ።

በሌላ በኩል ማህበረ ቅዱሳን አንዳንድ አባላቱ በሚያደርጉት ጫና ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን እድገት እንቅፋት እንደሆነ ይነገራል። ተሓድሶዎች የሚሉትን ትተን ወደ እውነታው ብንገባ ጸሐፊው የሚከተሉትን ዋና ዋና ስህተቶች / ችግሮች ተመልክቷል።

1. አንዳንዶቹ የማህበረ ቅዱሳን አባላት ስልታዊ አገልግሎት የሚባል አይታይባቸውም። በቤተ ክርስቲያን ማነኛውም አይነት ለውጥ እንዲደረግ አይፈልግም። ምእመኑን ባለው ሁኔታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማቅረብ ብቻ ይጥራሉ። ይህም ማለት ስህተቶች እንኳን ካሉ እነርሱን ትክክል ለማድረግ የሚያስችል ነገር ይፈልጋል እንጂ ቀኖናዊ ለውጥ መደረግ ይችላል የሚል አስተሳሰብ እንደሌለ ጸሓፊው ተረድቷል። በተለይ በአንዳንድ በመጽሓፍ ቅዱስ እውቀት የሌላቸው አባላት።
2. ትውፊት በሚል ሰበብ የኢየሱስስ ስም መጥራት ይከብዳቸዋል። ወይንም ኢየሱስ ያለ ሁሉ ፕሮቴስታንት እስኪመስል ድረስ ይመለከቱታል። የቤተ ክርስቲያን መጽሓፍት ግን ቅዳሴውም ኪዳኑም ድርሳኑም ሰአታቱም ኢየሱስ ክርስቶስ መድሃኒዓለም እያሉ በእየቦታው ይጠሩታል። ይህ ነገር ቀላል ሊመስል ይችላል ግን አይደለም አዳኝ የሆነውን ስም መጥራት የማነኛውም ክርስቲያን መንፈሳዊ ግዴታና ሓብት ነውና። ኢየሱስ የሚለው ስም የክርስቲያኖች እንጂ የሌሎች መለያ አይደለም።
3. መናፍቃኑ የቅዱሳንን ነገር እንዳቃለሉት የታወቀ ነው በአንጻሩ ደግሞ የማህበራችን ሰዎች በአብዛኛው ጊዜ ስብከቱም መዘሙሩም ንግግሩም ሁሉ ስለ ቅዱሳን እንዲሆን ይፈልጋሉ። ምክንያቱ ምን አልባት ቅዱሳንን የሚያቃልሉ ፕሮቴስታንቶች ያሰገቡትን አስተሳሰብ ለማሸነፍ ይመስላል። ሆኖም ስለ ቅዱሳን መሰረታዊ ነገር ከተያዘ መሰበክ መታወቅ ያለበት እግዚአብሔርና ትእዛዛቱ ቸርነቱ ምህረቱና ፍርዱ ነው።
4. ማህበረ ቅዱሳን እራሱ ያላጸደቀውን ወይም ከማህበሩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ሰባኪ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሰው በጥርጣሬ ይመለከታል። ምንም እንኳን በመዋቅር ደረጃ በሰንበት ት/ቤት ማደራጃ መምሪያ ስር ቢሆንምና በቲዎሪ ደረጃ ለተቀዋማዊ ስርዓት ታዛዥ ቢመስልም በፕራክቲካል ግን የራሱን አጥር አጥሮ በዚያ የሚጓዝ ነው። እባብ ያየ በልጥ ይደነግጣል እንደሚባለው ሁሉንም ሰው በጥርጣሬ አይን መመልከት ግንኙነትን በጣም ያሻክራል። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መተማመን እንዳይኖር ያደርጋል።

**የተሐድሶ ምንነት**

ተሃድሶ በሁለት ትርጉሞች ሊፈታ ይችላል አንደኛ ትርጉሙ ማሻሻል ሲሆን በሌላ መልኩደ ግሞ መለወጥ፡ አዲስ ማድረግ የሚለውን ሃሳብ ያስተላልፋል። መሻሻል በሚለው ትርጉሙ የተፋለሰውን ማስተካከል የጠፋውን ማቃናት የደከመውን ማበርታት ነው። መለወጥ በሚለው ትርጉሙ ሙሉ በሙሉ የተሳሳተውን ሃሳብ መተካት አዳዲስ ሃሳቦችን ማስገባት በአዳዲስ ሃሳቦች መመራት አዲስ ሃሳቦችን እንደመመሪያ መቀበልን ያመለክታል።

ተሃድሶ በሰዎች ላይም ይሁን በተቋማት ላይ ይካሄዳል። ለምሳሌ የፓለቲካ ፓርቲዎች የያዙት የኢኮኖሚና ይፓለቲካ አካሄድ የማያዋጣ ከመሰላቸው ወይንም አካሄዳቸው የተሳሳተ ከመሰላቸው ታድሶዎ ያደርጋሉ። ተሃድሰው ፍጹም መለወጥ ሊሆን ይችላል ወይንም ደግሞ መሻሻሎችን የያዘ ሊሆን ይችላል። ሰዎች ሃሳባቸውን ሊያሻሽሉ ሊያስተካክሉ ወይንም ደግሞ ሙሉበሙሉ በአዲስ ሊለውጡ ይችላሉ።

ተሃድሶ በመንፈሳዊው ሃሳብ ግን እንዲሁ የሚደረግ አይደለም ምክንያቱ ደግሞ መንፈሳዊው አለም መመሪያው የእግዚአብሄር ቃል መሪው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ። ከመመሪያውና ከመሪው ጋር መማከር በመሪውና በመመሪያው መደገፍና መታመን ያስፈልጋልና።

ቤተ ክርስቲያን እንደማነኛውም ተቋም ሰዎች ያሉባት ናት መሪዋ መንፈስ ቅዱስ መመሪያዋ የእግዚአብሄር ቃል ቢሆንም ቅሉ የሰዎች ሃሳብና ስራንም ታስተናግዳለች። በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሓዋርያት ጌታ ያስተማራቸውን እምነቶች በማስተላለፍ ቤተ ክርስቲያንን እንድትሰፋ አድርገዋል። እነርሱን የተከተሉ ቅዱሳን አበውም ሃይማኖትን እያጸኑ ስርአትን እየሰሩ እስከ ዛሬ አድርሰውልናል። በጎዎቹና መንፈስ ቅዱስን መሪያቸው ያደረጉ እንደነበሩ ሁሉ የራሳቸውን ሃሳብና እምነትም ሲያራምዱ የነበሩ ሰዎች አልነበሩም ማለት አይቻልም።

**ዛሬ ያሉ የተሃድሶ ሃሳብ አይነቶች**

በአሁኑ ጊዜ ተሃድሶዊያን ብዙዎች ናቸው። ፍጹም ኦርቶዶክሳዊያን ከሆኑጀምሮ እስከ ፍጹም ፕሮቴስታንት ድረስ ተሃድሶዎች አሉ። አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኖረው አድገው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን እምነቷንና ስርትዋን ተምረው አልጥማቸው ሲል እና እነርሱ እንደፈለጉት ስላልሄደ ቤተ ክርስቲያንን ለቀው ከሌሎች ጋር የተቀላቀሉ አሉ። እነዚህ ሰዎች ስላላመኑበት ሊቆዩ አልፈለጉም ስለዚህም በመውጣታቸው መልካም አደረጉ። ቤተ ክርስቲያን አንድም ሰው እንዲጠፋ ባትፈልግም እንኳን የማያምኑ ሰዎች ግን መለየታቸው አግባብ እንደሆነ ትናገራለች። ኑፋቄ ያለባቸውንም አውግዛ ትለያለች።

አብዛኛው ተሃድሶዎች በአንጻሩ ከቤተ ክርስቲያን መውጣት የሚፈልጉ አይደሉም። ይህም አንዳንዶቹ ለአላማቸው ማሳኪያ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ከልብ የቤተ ክርስቲያንን መሻሻል እንጂ የሃይማኖት ለውጥን ስለማይፈልጉ ነው። ሁለቱን የተሃድሶ አይነቶች አላማቸውና ምንነታቸውን እንደሚከተለው እናያለን።

1. **ፕሮቴስታንቱ ተሃድሶ**: ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶዎች በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የነበሩ አሁንም ሊኖሩ የሚችሉ ሰዎች ያሉበት ሲሆኑ እምነታቸው ከፕሮቴስታንት ጋር አንድ ነው። ሙሉውን የእግዚአብሄርን ቃል ከመቀበል ይልቅ እንደ ፕሮቴስታንቶች ቁንጽልና አንድን ሃሳብ ብቻ ይዘው የሚሄዱ ናቸው። የሚለዩት እነዚህ ኦርቶዶክሥ ነን ሲሉ እነዚያ ፕሮቴስታንት መሆናቸው ነው። አንዳንዶች በምሽትና በድብቅ ከፕሮቴስታንቱ ጋር አምልኮ የሚፈጽሙ ከነርሱ ጋር መልእክት የሚቀያየሩ፡ የበጀት ድጎማ የሚደረግላቸው ናቸው። እነዚህ ተሃድሶዎች አላማቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጠ መቆየትና በሚችሉት መጠን የእነርሱን አስተሳሰብ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስገባት ነው። ግባቸው ቢችሉ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ ጭምር መቀየር እና የፕሮቴስታንት እምነት በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ነው።

   የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አባላት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ከተነቃባቸውና ቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደማያዋጣቸው፡ ቦታ እንደማይኖራቸው ካወቁ ሳያወላውሉ ወዲያውኑ ከፕሮቴስታንቶች ጋር ሄደው ይቀላቀላሉ።

   በነገረ ድህነት በጥምቀት በቅዱስ ቁርባን በእምነትና በስራ ስለሚገኘኝ ጽድቅ ስለክህነት ስለንስሃ ስለቅዱሳን ስለምንኩስና በመሳሰሉ አስተምህሮዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ከኦርቶዶክስ የወጣ ትምህርትና ከፕሮቴስታንት አንድ የሆነ እምነት ያምናሉ። ኦርቶዶክስ ነን የሚሉት ሃይማኖት ለውጠዋል እንዳይባሉና ህዝብ ለመንጠቅ እንዲመቻቸው ብቻ ነው።

   እነዚህኞቹ ተሃድሶዎች ቤተ ክርስቲያንን ፊት ለፊት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚተቹ ያሳለፈቻቸውን ፈተናዎች ከመናገር ይልቅ ለማተላላትና ለማጣጣል የሚሰሩ ናቸው። ለሰው ይምሰል ብቻ ቤተ ክርስቲያንን ታሪካዊት ናት እናታችን ናት ይበሉ እንጂ ንግግራቸው ሁሉ የሰው ልብ ለማጥመድ ብቻ የሚያደርጉት ነው። በተግባር ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሲቆሙ አይታዩም።

   በአብዛኛው የዚህ ቡድን ደጋፊዎች ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ዶግማና ቀኖና በሚገባ ያልተማሩ ሰዎች እንዲሁም የአስተሳሰብ ግጭት የተፈጠረባቸው ሰዎች ናቸው። በተለይም በክህነት የሚያገለግሉ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና እምነት ያልተማሩ ሰዎች የዚህ አስተሳሰብ ተጠቂዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ጥንቆላ እንዲቆም በእየቀኑ እንደማይሰበክ ድግምተኛና ጠንቋይ የሆኑ መርጌቶች ወደ ዚህ ቡድን ከገቡ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ድግምተኛ ናት ብለው ሲሰድቡ ይታያሉ እነዚህም ብዙዎች የዚህ አባል ከሆኑት ውስጥ ይመደባሉ።

2. **ኦርቶዶክስ ተሃድሶ**: እነዚህም በራሳቸው በልዩ ልዩ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ለውጥ ያስፈልጋል ብለው የሚያስቡ ናቸው። ለውጥ ስንል የአስተዳደር ለውጥ ማለታችን አይደለም። የአስተዳደር ለውጥ እንዲኖር አብዛኛው ሰው ይፈልጋል። እነዚህ ተሃድሶዎች የሚፈልጉት የቀኖናና የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። እነዚህን ራሱ በሁለት ይከፈላሉ።
   a. አንደኛዎቹ ወገኖች ሙሉበሙሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ዶግማ የሚቀበሉ ነገር ግን በስርአተ ቤተ ክርስቲያን እና በገድላት ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ናቸው። በቀኖና ረገድ ቤተ ክርስቲያንን ዘመናዊ ለማድረግ በእነርሱ አስተሳሰብ ወንጌልን በቀላሉ ለህዝብ ለማስተላለፍ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ የስርአት መሻሻሎችን ማድረግ አለባት ብለው ያምናሉ። ለምሳሌ ለምእመናኑ ነጻነት የሚሰጡ ነገሮችን ማድረግን ይፈልጋሉ። ጫማ አድርጎ ቤተ ክርስቲያን

ውስጥ እንደመግባት ፡ የፈለጉትን እንዲበሉ መፍቀድ፡ የጸሎቱን ይዘት ማሳጠር በአላትንና አጽዋማትን መቀነስ። ወንጌልን ለማዳረስ በሚል ሳቢያ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ተጠቅሞ መዘመርን ይደግፋሉ።

ገድላትና ታምራትን በመሰረታዊነት ቢቀበሉም አግልግሎታቸው ላይ ግን ገደብ እንዲደረግ ይፈልጋሉ። ለምሳሌ ብዙ ጊዜ ተወስደው የሚነበቡት እንደ ታምረ ማርያም አይነት መጻሕፍት ከአገልግሎታቸው መነሳት አለባቸው ብለው ያምናሉ። ከተነበቡም የመነበቢያ ጊዜቸው ውስን እንዲሆን ይፈልጋሉ።

ь. ሁለተኞቹ ኦርቶዶክስ ተሃድሶች፡ እነዚህ ተሃድሶዎች ለማለት ቢከብድም የማስተካከያ ሃሳብ የሚያቀርቡ የቤተ ክርስቲያንን ክብርና ማንነት ስርአትንም ለማስጠበቅ የሚተጉ ናቸው። እንደ ዳንኤል ክብረት ገለጻ ቤተ ክርስቲያን ህዳሴ ማድረግ (ወደ ቀድሞ ክበሯ መመለስ) አለባት ብለው የሚያስቡ ናቸው። ለውጡም ለሰዳቢዎች ምክንያት የሆኑ እና ትክክል ያልሆኑ ነገሮች ይታረሙ የሚል ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትፈተነው በሌሎቹ ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያንም ድክመት ጭምር ነው ብለው የሚያስቡ ናቸው። በመሆኑም ድክመቶችዋ የሆኑት ነገሮች እንዲስተካከሉ የሚፈልጉ ናቸው።

እነዚህኞቹ ለውጥ ፈላጊዎች ለቤተ ክርስቲያንና ለክርስቲያናዊ ትውፊቷ የሚቆረቆሩ ከመሆናቸውም በላይ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚተማመኑ ሲኖዶሱ ራሱ የለውጡ መሪ እንዲሆን የሚማጸኑ ናቸው። ቅዱስ ሲኖዶስ ያላጸደቀውን ቀኖናም አይፈጽሙም።

**ለውጥ ለቤተ ክርስቲያን ወይስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ደባ**

ምንም እንኳን እኔ ክፉ ነገር አደርጋለሁ የሚል አካል ባይኖርም ዛሬ ሁሉም የተዘረዘሩት የተሃድሶ አይነቶችም በእርግጥ ለቤተ ክርስቲያን ነው የሚሰሩት ወይስ ለራሳቸው አጀንዳ ብሎ ሰው መጠየቁ አይቀርም። አንድን አካል ለሌላ አካል ነው የሚሰራው የሚለው መመዘኛው የተጠቃሚውን አካል መብቶች ሲያከበርና ፍላቶቱን ለማሟላትና ለመፈጸም ሲጥር ነው።

በቤተ ክርስቲያን እንሰራለን በማለት ብቻ ለቤተ ክርስቲያን ይሰራሉ ማለት አይቻልም። አንድ ለቤተ ክርስቲያን እሰራለሁ የሚል አካል ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታምነውን ነገር የመናገር ባይችል ያለመስደብ ግዴታ አለበት። ስርዓትዋንና ዘይቤዋን መረዳት ተገቢና አስፈላጊ ነው። ለእርስዋ እስከሆነና በእርስዋ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ አካል ስርአተ ቤተ ክርስቲያንን እና የሲኖዶስን ውሳኔዎች መጠበቅ ሃላፊነት አለበት። ያን ሳያደርግ ለቤተ ክርስቲያን እሰራለሁ ቢል አባባሉ የተምታታ ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ስርአት ባለው መልኩ ጥያቄዎችን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ከአንድ ለቤተ ክርስቲያን እሰራለሁ ከሚል አካል የሚጠበቅ ነው። ችግሮችን ድክመቶችን እና ትችቶችን እያዩና እየሰሙ ለሚመለከተው ክፍል አለማቅረብም ለቤተ ክርስቲያን እሰራለሁ ከሚል አካል አይጠበቅም። አንድ ልጅ ቤተሰብ ውስጥ ያለውን ችግር ለወላጆቹና ለታላላቆቹ እንዲፈታ መጠቆም የሚገባው ነው። ቤተሰቡም ተወያይቶ ለልጁ ችግር ሳይሆን ችግር የመሰለውን ያብራራለታል በትክክል ችግሮች ካሉ ደግሞ ይፈታል። በቤተ ክርስቲያንም እኛ ችግር የመሰለንን ሁሉ ለቅዱስ ሲኖዶስ ማቅረብ ተገቢ ሲሆን ቅዱስ ሲኖዶስ ደግሞ እንደ የበላይ አካልነት ለልጆቹ ተገቢውን መልስ መስጠት ተገቢ ነው።

በመሆኑም ለውጥ ያስፈልጋል የሚሉ አካላት ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ስራ መስራታቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ለቤተ ክርስቲያን የሚሰሩ ወገኖች የቤተ ክርስቲያንን ክብር አስጠብቀውና ጠብቀው ህጉ በሚፈቅደው መልኩ ተገቢው ለውጥ እንዲመጣ ይጠራሉ። በለውጥ ስም በቤተ ክርስቲያን ላይ ደባ ያደቡ ሰዎች በሌላ መልኩ ህግና ስርዓት በማይፈቅደው መልኩ ቤተ ክርስቲያንን የሚያሰድብ ምእመናንን የሚያሳቅቅ ነገር በእየለቱ ይሰራሉ።

## በቤተ ክርስቲያን የትኛው ተሃድሶ ያስፈልግ ይሆን?

ባለፈው ጽሑፋችን ስለማህበረ ቅዱሳን መልካምና ደካማ ጎኖች ስለተሃድሶዎችና ፍላጎታቸው ተመልክተናል። በተለይም ደግሞ ተሃድሶዎች ከእምነታቸው አንጻር ፕሮቴስታንትና ኦርቶዶክስ ተብለው እንደሚከፈሉ። ፕሮቴስታንት ተሃድሶዎች ግባቸው ተዋህዶን ወደ ፕሮቴስታንትነት መቀየር ሲሆን ካልቻሉ ደግሞ ምእመናንን መንጠቅና ወደ ፕሮቴስታንትነት መቀየር እንደሆነ ተመልክተናል። ኦርቶዶክስ ተሃድሶዎች ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ ለውጥ ያስፈልጋል የሚሉ እንደሆኑ አይተናል።

__ከዚህ ቀጥሎ እነዚህ የተሃድሶ አይነቶች ለቤተ ክርስቲያን የሚፈይዱት ነገር ካለ እንመረምራቸዋለን።__

**ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ**: ይህ አካል ከዶግማው ጀምሮ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የሌለው በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ይኖረዋል ማለት ከባድ ነው። የኦርቶዶክስ ተዋህዶን እምነት የሚቀበል ለመምሰል ከሃይማኖት አበውና ከድጓ ከልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መጻህፍት እየጠቀሱ ይናገራሉ፡ በግእዝ ልሳንም ጥቅሶችን ያቀርባሉ። ሆኖም ግን የሚጠቅሷቸውን መጻህፍት እንኳን በአግባቡ አይቀበሏቸውም። አስቀድሞ እንደተናገርሁት እነዚህ ተሃድሶዎች አባላቱ በኦርቶዶክሳዊ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በቂ የመጽሐፍ ቅዱስና የነገረ መለኮት እውቀት የሌላቸው ወይንም ደግሞ በመንፈሳዊ ተቋማቱ ገብተው የንጽጽር ትምህርት ሲሰጣቸው በዚያው ተምታትቶባቸው የሚቀሩ ቲዎሎጂያን ናቸው።

የእነዚህ ሰዎች ጥያቄ የፕሮቴስታንት ጥያቄ ነው። ሊያደርጉ የሚፈልጉት ተሃድሶም ፕሮቴስታንቶች ቤተ ክርስቲያን ብትሆን ከሚፈልጉት ጋር ተቀራራቢ ነው። የዚህ ጽሁፍ ጸሓፊ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ተገናኝቶ ማወቅ እንደቻለው ወደ 30 የሚጠጉ ጥያቄዎችንና ትችቶችን በቤተ ክርስቲያን ላይ ያቀርባሉ። በሚያነሷቸው ጥያቄዎች ሁሉ አስተምህሯቸው ከፕሮቴስታንት ጋር አንድ ዓይነት ነው። እምነታቸውን በጥቂቱ ለመዳሰስ ያክል የሚከተሉትን ዝርዝሮች መመልከት ይቻላል።

1. የቤተ ክርስቲያንን የስላሴ አስተምህሮ ከፍለው ያምናሉ።
2. ክብር ይግባውና ኢየሱስ ክርስቶስን ይለምናል የሚሉ ናቸው እርሱ ግን በስሜ ትለምናላችሁ እንጂ እኔ ስለእናንተ አልለምንም አለን ዮሓ 16:26
3. መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ጭምር ይወጣል የሚል የካቶሊክ እምነት ያምናሉ ጌታ ግን መንፈስ ቅዱስን ከአብ የሚወጣ ብሎ አስተማረን ዮሓ 15:26
4. ድህነት በአጭር ጊዜ የሚፈጸም እንጂ በህይወት ጉዞ የሚገኝ ነው ብለው አያምኑም መጻህፍት ግን መዳናችንን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ እንፈጽም ብለው ነገሩን ፊሊ 2:12
5. ድህነት በእምነት ብቻ ይገኛል ብለው የሚያምኑ ናቸው ሐዋርያት ግን እምነትና ስራ ለድህነት ያበቃሉ ብለው ተናገሩን ያእ 2:26
6. ስጋውና ደሙ የጌታ ስጋና ደም ሳይሆን መታሰቢያ ብቻ ነው ብለው ያምናሉ ጌታ ግን ይህ ስጋየ ነው ብሎ ነገረን ማር 14: 12
7. የጌታን ስጋ መቀበል ለድህነት ግድ አይደለም ይላሉ መጽሐፍ ግን ስጋውን ያልበላ ደሙንም ያልጠጣ የዘለአለም ህይወት የለውም አለን ዮሓ 6:54
8. ጥምቀት ለመዳን የግድ አይደለም ለክርስትናችን ማረጋገጫ እንጅ ይላሉ ጌታ ግን ያመነና የተጠመቀ ብቻ ይድናል አለን ማር 16:16
9. ሁሉም ሰው ካህን ነው ብለው ያምናሉ ጌታ ግን ሐዋርያትን ብቻ መርጦ ስልጣን ሰጣቸው ማር 3:15 ማቴ 18:18
10. የአዋጅ ጾምን ይቃወማሉ ሐዋርያት ግን የታወቀ የጾም ወቅት ነበራቸው ጌታም የፈሪሳዊያንን የአዋጅ ጾም ሳይሆን አጿጿማቸውን ነው የነቀፈው ሐዋ 27:9 ዘካ 8:19 ማቴ 6:16
11. ትውፊት አያስፈልጉም ባዮች ናቸው መጽሓፍ ቅዱስ ግን በትውፊት የተገኙ ነገሮችን መዝግቦ ይዞ ይገኛል ሐዋርያትም ትውፊታቸውንና ወጋቸውን እንድንይዝ መከሩን 2ኛ ተሰ 2:15
12. ድንግል ማርያምን ከጌታ ሌላ ልጆች አሏት ይላሉ መጽሓፍ ቅዱስ ግን ማርያም ሌላ ልጆች ነበሯት አይልም /ሙሉ መጽሓፉ/
13. የቅዱሳንን መታሰቢያ ማድረግን ይከለክላሉ/ይነቅፋሉ መጽሓፍ ቅዱስ ግን የጻድቃን መታሰቢያ ለበረከት ነው ይላል ምሳ 10:7
14. ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ የተረሱ ናቸው ይላሉ መጽሓፍ ቅዱስ ግን የጻድቃን መታሰቢያል ለዘለአለም ይኖራል ይላል መዝ 112:6
15. ቅዱሳንን ማመስገን ባእድ አምልኮ ነው ይላሉ መጽሓፍ ቅዱስ ግን ጻድቃን ሆይ ደስ ይበላችሁ ለቅኖች ምስጋና ይገባል ይልባቸዋል መዝ 33:1
16. ለቅዱሳን ክብር መስጠት የጸጋ ስግደት መስገድ ሓጥያት ነው ይላሉ ጌታ ግን ለደጉ ካህን ከእግሮችህ በታች ይሰግዱልሃል ይለዋል ራእ 3:9
17. ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ አያውቁም ይላሉ መጽሓፍ ግን የሚሞተው የሰው ስጋ እንጅ ነፍስ ዘለአለማዊ እንደሆነች ይነግረናል መክ 12:7
18. ሰው ከሞተ በኋላ መለመን አይችልም ይላሉ ጌታ ግን እንኳን ቅዱሳን ሃጥአን እንኳን እንደሚለምኑ አስተማረን ሉቃ 16:19 25
19. ለሞተ ሰው መጸለይ ትርፉ ድካም ብቻ ነው ይላሉ መጽሓፍ ግን ማንም ስለ ወንድሙ ቢለምን ይማርለታል ይላል 1ኛ ዮሓ 5:16
20. ስእል አያስፈልግም እንዲያውም ጣኦት ነው ይላሉ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ግን ቅዱሳት ስእላት ነበሩት 1ኛ ነገ 6:29

21. ታቦት አስፈላጊያችን አይደለም ይሉናል ቤተ ክርስቲያን ግን በሰማይ ባለው ቤተ መቅደስ አምሳያ ራሷን እንዳነጸች ማስተዋል አይፈልጉም ራእ 11:19
22. ገድላትና ድርሳናት የሰዎችን ታሪክ ስለሚተርኩ አስፈላጊ አይደሉም ይሉናል። መጽሓፍ ቅዱስ ግን የቅዱሳንን ገድል ጽፎ እናገኘዋለን። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ በኩል የሚያደርገውን ጸጋም ያስተምረናል። ሓዋ 5:15 ዕብ 13:7
23. ቃል ኪዳን የሰዎች ፈጠራ ነው ለድህነትም ሆነ ለክርስትና ጥቅም የለውም ይላሉ መጽሓፍ ግን እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጣቸው ቃል ኪዳን ለትውልዳቸው እንደሚተርፍ ጽፎ ያሳየናል። ዘዳ 8:18 መሳ 2:1 1ኛ ነገ 11:32
24. ተዋህዶ በልሳን ስለማትናገር መንፈስ ቅዱስ የለባትም ይላሉ በመጽሓፍ ቅዱስ ግን ሁሉም ክርስቲያኖች በልሳን ይናገሩ ነበር አይልም። 1ኛ ቆሮ 14:26 ዛሬ የሚነገረው ልሳንም የመንፈስ ቅዱስ እንዳልሆነ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። http://www.cyberethiopia.com/warka4/viewtopic.php?t=37961&sid=c138a7393a2057263b0f371c93c84a58
25. ስለጸበል ስለቅዱስ መስቀል ስለገዳማትና ስለምንኩስና ኦርቶዶክስ ስህተት ነው ብለው ይናገራሉ። እኛ ግን አበው ያሳዩንን መጽሓፍ የተናገረንን ይዘን እንምናለን።

ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶዎች መጽሓፍ ቅዱስን በሚገባ ያልተረዱ በቃለ እግዚአብሔር ያልበረቱና አለቆቻቸው ፕሮቴስታንቶች የነገሯቸውን ብቻ የሚናገሩ ናቸው። በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ሙሉውን የመጽሀፍ ቃል ላለማመን ምክንያት የሚሰጡና ከእውነትም መንገድ ፈቀቅ ያሉ ናቸው። በተዋህዶ ላይ ጥላቻ አለባቸው። ኦርቶዶክስ ተዋህዶን እንደ አሪት እምነት ይቆጥራሉ። አንድ የእነዚህ ቡድኖች አባል የሆነ ሰው እዚህ ከተማ ቤተ ክርስቲያን አለን ብሎ ጠየቀኝ እኔም አዎ እኛ ቤተ ክርስቲያን አለን አብረን መሄድ እንችላለን ስለው አይ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ነው የምፈልገው ያለኝ ለእነዚህና ለመሰሎቻቸው ማስረጃ ነው።

እነዚህ ሰዎች በትክክል ዶግማዊ ችግር ቢኖርባቸውም በሃገራችን ካሉ አባሎቻቸው የምንማራቸው ደግሞ ጠንካራ ጎኖች አሏቸው። እነዚህም

1. የሚያምኑበትን ነገር ደፍረው እንዲናገሩ ማስተማራቸውና ማበረታታቸው ። ዛሬ ፕሮቴስታንት በቁጥር ሊበዛ የቻለው አስተምህሮው ትክክለኛ ስለሆነ አይደለም። አስተምህሮው /ዶግማው መጽሓፍ ቅዱስን ለሚያውቅ ሰው ብዙ የሳቱ ነገሮች እንዳሉት የሚታወቅ ነው። ትልቁ ጠንካራ ጎናቸው የሚያስተምሯቸውን ሰዎች ስለሚያስተምሩት ነገር በቂ ግንዛቤ በመስጠት ሳይፈሩና ሳያፍሩ እንዲናገሩ በማደፋፈራቸውና በዘመናዊና ሳይኮሎጂን በማጥናት ለሌሎች መናገራቸው ነው።
2. አባሎቻቸውን በጥብቅ ክትትል መከታተላቸው። ለአንዳንዶች ነጻነት ባይሰጣቸውም ፕሮቴስታንቶች አባሎቻቸው የሚገቡበትንና የሚወጡበትን ይቆጣጠራሉ። ከፕሮግራሞቻቸው ላይ እንዳይቀሩ ትኩረት ሰጥተው ይቀሳቀሳሉ።

**ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ለቤተ ክርስቲያን?**

ተዋህዶ እምነትዋ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አባቶች የሚያምኑት ነው። እነዚህ አባቶችም ያምኑት የነበረው ከሐዋርያት በመጽሓፍና በትውፊት ያገኙትን ነው። ተዋህዶ ስለእግዚአብሔር አብ አምላክነት ስለስግው ቃል ፈጣሪነት ስለመንፈስ ቅዱስ ምልኡ በኩልሄነት በአጠቃላይ ስለስላሴ ከሐዋርያት የተለየ እምነት የላትም።

ከላይ የተጠቀሱት ጸረ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትምህርቶችን ቢይዙም እንኳን ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ ወይንም ለመቀየር አላማ አላቸው። የጠቀስናቸውንና ሌሎች ያልተጠቀሱ ለውጦችን በቤተ ክርስቲያን እንዲደረግ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ይህንን እሽ በጎ ብሎ ሊቀበል የሚወድ ኦርቶዶክሳዊ ማን ይሆን? እነዚህን መተባበር ማለት የክርስቶስን ማንነት መካድ የቅዱሳንን ነገር መተው ቤተ ክርስቲያን ያላትን እውነት ወደ ኋላ ሄዶ አለማየት ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በምንም ይሁን በምን ማንም ይበል ማን ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ አያስፈልጋትም። ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ታድርግ ማለት ቤተ ክርስትያን ስትመሰረት ጀምሮ ስህተት ነበረች ማለት ነው። ከእውነት የወጣ ሃይማኖት አባቶች ያላስተማሩን እምነት ይኑረን ማለት ነው።

በአንጻሩ በቤተ ክርስቲያን ፕሮቴስታንቶች እና እነርሱ ለወለዷቸው ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶዎች ለሚያነሱት ጥያቄዎችና ትችቶች መልስ የሚሰጥ የቤተ ክርስቲያን አካል አለመኖሩ ሊታሰብበት የሚገባ ነው። ከ1980 ዎቹ ጀምሮ ብዙ ሊቃውንትና ሙሁራን በእየድርሻቸው መናፍቃን ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል ሆኖም ግን በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ቋሚ መረጃ ሊሆን የሚች ማጣቀሻ ሊሆን በሚችል ሁኔታ የተዘጋጀ መልስ የለም። የቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ጥያቄዎች ሲነሱ እንዲሁ ሌላ አካል

እንዲመልስ ዝም ብሎ ማየት የለበትም ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ማስረጃዋን እያጣቀሰ ለምእመናኗ ማቅረብ አለበት እንጂ። ይህ በተለይ በመድበል መልክ የሚዘጋጅና ማነኛውም ምእመን ሊያገኘው በሚችል ሁኔታ መዘጋጀት አለበት።

## <u>አንዳንድ ሰዎችና ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ</u>

በቤተ ክርስቲያን እየኖሩ በእምነት ግን የሌሉ ከተዋህዶ ደሞዝ እየተቀበሉ ለፕሮቴስታንት የሚሰሩ ሰዎችን በተለያዩ ጊዜያት ተመልክተናል። ጊዜያቸው ሲደርስ በውድም በግድም ወጥተዋል። የሚመለሱትን መምከሩ እንዳለ ሆኖ እነዚህን ሰዎች መታገሱና ቤተ ክርስቲያን እንዲቆዩ መፍቀዱ ሌላ እሾህ እንዲያበቅሉ እና ብዙ ሰዎችን እንዲወጉ እድል መስጠት ነው። የታወቁ ሰዎች ስለሆኑ ታዋቂ መምህራን ሰባኪያን ወይንም ቀሳውስት ስለሆኑ በቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት ጉዳይ ችላ የሚባል ሰው ሊኖር አይገባም። ህጸጽ ያለባቸውን በሊቃውንት እያስመከሩ መለየት የቤተ ክርስቲያን አንዱ ተግባር ነው።

አንዳንዶች መምህሮቻቸው ወደ ኑፋቄ ወደ ክህደት ሲሄዱ መምህሮቻቸው በመሆናቸው እነርሱን ደግፈው የሚቆሙና ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ጋር የሚወግኑ አሉ። እውነታውና ልናደርገው የሚገባን ግን ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅምን ነገር ብቻ እንከተል። ከሰዎች ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን ከእኛ ፍላጎት ይልቅ ለቅዱስ ቃሉና ለኢየሱስ ክርስቶስ እንወግን።

## ኦርቶዶክስ ተሃድሶዎች

በአንደኛ ደረጃ ያስቀመጥናቸው ኦርቶዶክስ ተሃድሶዎች በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ዶግማ የሚያምኑ ሲኖዶሱ ቀኖና ማውጣት እንደሚችል ቀኖናውን መቀበልና ማክበር እንደሚገባ የሚያምኑ ናቸው። ሆኖም ግን በአንዳንድ ጉዳዮች ቤተ ክርስቲያን ስር ነቀል ለውጥ ማድረግ አለባት በለው ለውጥ የሚናፍቁ ናቸው። እነዚህ ቡድኖች እንዳይገለሉ የሚፈሩ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ ለውጥ ብታደርግ የተሻለ ትጠናከራለች ብለው የሚያስቡ ናቸው። ህዝቡን ለመያዝና አብዛኛው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመን ንቁ ክርስቲያን ሆኖ እንዲቀጥል ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ጉዳዮች ዙሪያ ቀኖናዊ ለውጥ ብታደርግ ጥሩ ነው ብለው የሚናገሩ ናቸው። በአብዛኛው ጊዜ ፍላጎታቸውን በቀጥታ ባይናገሩም በእውቀት ዳብሯል ብለው ለሚያስቡት ሰው ግን ሃሳባቸውን ይገልጻሉ።

እነዚህ ቡድኖች እንደ ምሳሌ የሚወስዱት የእህት አብያተ ክርስቲያናትን የአምልኮ ስርአትና ነው በተለይም የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የአምልኮ ስርአት ብዙ ጊዜ ይጠቅሳሉ። የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በትምህርተ ሃይማኖት ደረጃ አንድ ሊባል የሚችል እምነት ያምናሉ በጣም ጥቂት ልዩነቶች ከመኖራቸው ውጭ ዶግማችንና እንዲሁም የቅዳሴው ጸሎት ይዘትም አንድ ሊባል የሚችል ነው። አብዛኛው ቀኖናቸውም እንዲሁ ይመሳሰላል። ለምሳሌ የክህነት አሰጣጣቸው፡ የጳጳሳት ስልጣናቸው፡ የቤተ ክርስቲያን አሰራራቸውና አከባበራቸው፡ የበአላት ቀናቸው፡ የጾም ጊዜቸው፡ የጾም አጿጿማቸው፡ የንስሃ አገባባቸው እና የመሳሰሉት የሚመሳሰሉ ናቸው።

በአንጻሩ በማህበር ሆነው በሚያደርጓቸው አምልኮዎች ላይ አንዳንድ ልዩነቶች ይለያያሉ። አብዛኛዎቹ ልዩነቶች በሚከተሉት ማጠቃለል እንችላለን

1. እነርሱ ላይ የሌሉ እኛ ላይ የሚደረጉ ጸሎቶች
2. እነርሱ ዘንድ የማይከለከሉ እኛ ላይ የሚከለከሉ ስርአቶች
3. እነርሱ የሚያደርጓቸው እኛ የማናደርጋቸው ስርአቶች
4. እኛ የምናደርጋቸው እነርሱ የማያደርጓቸው ስርአቶች

በአብዛኛው የልዩነቶች ምክንያቶች ሊሆኑ የሚችሉ ተብለው የሚጠቀሱ የሚከተሉት ናቸው

1. ኢትዮጵያዊያን ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ኦሪትን አምነው ይኖሩ የነበሩ መሆናቸው
2. ኢትዮጵያውያን በነጻነት አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲፈጽሙ መኖራቸው በአንጻሩ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ለብዙ አመታት በእስልምና ተጽኖ ውስጥ መቆየትዋ
3. ግብጾች ስርአታቸው ላይ በሲኖዶስ ድንጋጌ መሰረት በቅርብ ጊዜ ለውጥ ማካሄዳቸው
4. የግብጽ ኦርቶዶክስ ብዙ ፈተናዎችን አሳልፋ አሁን በውስጣዊ መረጋጋት ላይ መሆንዋ ሊቃውንቶችዋ በተለይም ፓትሪያርኳ ቤተ ክርስቲያኒቷን በዘመናዊ መልኩ መምራታቸው ለአዲሱ ትውልድ ስለሃይማኖቱ በቀላሉ ሊያገኘው የሚችል መጻህፍትን መጻፋቸው

እነዚህ ተሃድሶዎች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ልዩ ልዩ ክፍል አላቸው እነዚህንም እንደሚከተለው እንመለከታለን:

### *ሀ  እህት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ቀለል የሚሉ ስርአቶች እኛም ላይ ተፈጻሚ ይሁኑ*

1. ኮፕቶች ጫማ አድርገው ስለሚገቡ እኛም አድርገን ቤተ ክርስቲያን እንድንገባ ይፈቀድ፡
2. ኮፕቶች ላይ የበአላት ቁጥር ስለሚቀንስ እኛም ጋር ይቀነሱ፡
3. ኮፕቶች የማይጠቀሟቸው እንደ ታምረ ማርያም ያሉ መጻህፍት እኛ ላይም ከአገልግሎት ቢቀሩ

### *ለ  በብሉይ ኪዳን የተከለከሉ እና በቤተ ክርስቲያን በባህልና በስርአት የተከለከሉ ነገሮች ይቅሩ*

አንዳንድ ጉዳዮች በብሉይ ኪዳን በግልጽ የተከለከሉ በሌሎች ክርስቲያኖች ዘንድ ክልክል ያልሆኑ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን በቀኖና ውስጥ የተካተቱ ወይንም በልማድ የሚደረጉ ጉዳዮች አሉ። እነዚህን ጉዳዮች ተሃድሶዎች ቀለል ወዳለው መንገድ እንዲሄዱ ይፈልጋሉ። ለምሳሌ

1. ሴቶች በወር አበባ ጊዜም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይገቡ መከልከል የለባቸውም ይላሉ

2. ስጋዊ ጉዳት የማያመጣ ከሆነና ባህላችን የሚፈቅደው ከሆነ ማነኛውንም ነገር ባርከን መብላትን ቤተ ክርስቲያን አትከለክልም ለማዳችን እንጂ ይላሉ
3. ክርስቲያኖች ተራክቦ ፈጽመውም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይገቡ መከልከል የለባቸውም ይላሉ

**ሐ ዘመናዊ ከማድረግ ጋር የሚያነሷቸው ጥያቄዎች**

1. በኦርጋን መዘመር ይፈቀድ: በኦርጋን መዘመርን ብቻውን ያወጣሁት ብቻውን ስለሚጠቅሱት ነው። እነዚህ አካላት በስፋት መዝሙርና የሙዚቃ መሳሪያን በተመለከተ በጻፉበት ዌብ ሳይት ላይ እንደጠቀሱት በልዩ ልዩ ጊዜያትም እንደሚናገሩት ኦርጋን በእኛ ኦርጋኖን ተብሎ ይጠራል ይላሉ። ይህ ከሌላ ወገን ጥናት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። በኦርጋኖን መዘመርን ደግሞ ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ መዝሙር መሳሪያዎች ባወጣው ቀኖና ላይ ይፈቅዳል ብለው ይከራከራሉ ለዚህም ሐመር መጽሔት የጻፈውን ጽሑፍ እንደ መረጃ አድርገው ያቀርባሉ። በሌላ በኩል የሓመር ጸሑፍ እንደሚያሳየው /ወይንም ጸሓፊው እንደተረዳው/ ኦርጋንና ኦርጋኖን የተለያዩ እንደሆኑ ነው። http://www.ethiopianorthodox.org/churchmusic/musicrelateddoc/synodos%202.pdf
2. በሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎች መዘመር ይፈቀድ: እነዚህ አካላት አሁን ስለሚጠቀሙበት ኦርጋንን በቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ስንጠቀምበት የኖርን ነው ቢሉም ሌሎች ዘመናዊ መሳሪያዎችን መጠቀምም እንዲፈቀድ ይፈልጋሉ። በእነዚህ መሳሪያዎች መዘመርን የሚፈልጉት ለምን እንደሆነ ሲጠየቁ መልካም ድምጽ ስለሚያሚያወጡና ቤተ ክርስቲያንን ዘመናዊ ለማድረግ ነው ይላሉ።

**መ ህዝብን ከመያዝ ጋር የሚነሱ ጥያቄዎች**

የሚከተሉት ጥያቄዎች ብዙም ደጋፊ ያላቸው አይሆኑም እንኳን በእኛ ቤተ ክርስቲያን ይቅርና በሌሎች ኦርቶዶክሶችም ዘንድ ጥያቄውን የሚያነሱ ያሉ አይመስለኝም።ሆኖም አንዳንዶች የሚከተለውን ጥያቄ ሲያቀርቡ ይታያል

1. ከአጽዋማቱ ውስጥ የነነዌ ጾምን ሌላ ስም ብንሰጣት ለምሳሌ የኢትዮጵያ ጾም ብንላትና ስለአንድ ነገር ለምሳሌ ስለሓገራችን እያሰብን በአንድነት የምንጾመው ጾም ቢሆን
2. አጽዋማቱ በመብዛታቸው ብዙው ኦርቶዶክሳዊ እየጾመ አይደለም በመሆኑም የጾሞችን ቁጥር ብንቀንሰውና አብዛኛው ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን እንዲጾም ቢሆን

**የጸሓፊው አስተያየት እና እውነታዎች**

እነዚህ የቀረቡት ጉዳዮች ትክክለኛነታቸው እና ጠቀሜታቸው ምን ያክል ነው? ከቤተ ክርስቲያን እምነት ስርአትና ትውፊት አንጻርስ ምን ያክል ጥቅምና ጉዳት አላቸው የሚለውን እንመልከት።

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የራሱ የሆነ ባህልና ስርአቶች አሉት። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ በራሱ ይዟቸው የመጣ ትውፊቶች በህዝቡ ዘንድ ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው ባህሎች አሉት። ያ ባህል ከሃይማኖቱ ጋር እስካልተጋጨ ድረስ መጠበቁና ለትውልድ መተላለፉ ጠቀሜታ አለው። ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ወጣ ብለን በካቶሊኮች በምስራቅ ኦርቶዶክሶች እንዲሁም በፕሮቴስታንቶች ዘንድ የምናገኛቸው ልዩ ልዩ ባህሎች አሉ። እነዚህ ባህሎች ደግሞ ለሃይማኖቱ መጠበቅም ጥሩ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። የራሳችንን ትተን በሌላ ቤተ ክርስቲያን ያየነውን ሁሉ እናምጣ ማለት ማንነትን አለማወቅ ነው።

ቤተ ክርስቲያን አብዛኛው ስርአትዋ የተመረኮዘው እግዚአብሔርን ከማክበርና ራስን ዝቅ ከማድረግ አንጻር ነው። ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ጫማ አድርገን እንዳንገባ የከለከለችው በትህትናዋ እና በእምነትዋ ነው። እምነትዋ በጸሎት ጊዜ እግዚአብሔር አብሮኝ ይኖራል (ማቴ 18:16) ለሰሎሞን የገባውን ቃል ኪዳን እስከዛሬ ያጸናል እግዚአብሔር ወደ ቤተ መቅደሱ ይመለከታል (1ኛነገ 9:3) እግዚአብሔር የሚገለጥበት ቦታ ቅዱስ ነው (ዘጸ 3:5) የሚል ሲሆን ትህትናዋ ደግሞ ቅዱስ የሆነው እግዚአብሄር በረድኤት በሚገኝበት ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዴት ጫማ አድርጌ እገባለሁ ብላ ነው። ታዲያ ይህ እምነትና ትህትና ዘመኑ ስላደገ ኑሯችን ስለተሻሻለ ጫማ መግዛት ስለቻልን ብንለውጠው ጥሩ ይሆንን?

በአላት እግዚአብሔር በራሱ ወይንም በወዳጆቹ አማካኝነት ታምራት የተደረገባቸው ቀናት በመሆናቸው መታሰብ ይገባቸዋል። ለታምራቱ መታሰቢያን አደረገ እንዲል መጽሐፍ (መዝ 111:4)። በአላት የእግዚአብሔርን ቸርነት ምህረት ድል አድራጊነት የቅዱሳንን ተጋድሎ ጽናት መታሰቢያ በረከት የምናስብባቸው ናቸው። እነዚህ ደግሞ በእምነታችን እንድንጠነክር መልካም እንድናደርግ ፈተናን እንድናልፍ የሚረዱን ናቸው።

በአንጻሩ በሃገራችን በአል ሲባል በአብዛኛው ስራ ፈትቶ መቀመጥ የሚለውን ነገር የሚያመለክት ነው።በቋንቋው ራሱ በአል ሲባል ስራ ማቋረጥ እንደማለት ስለሆነ የመንግስት በአል እንዲባል። በእንግሊዘኛው ቋንቋ የተሻለ ቃል የሚጠቀም ይመስላል ሁለቱን የተለያየ ትርጉም ይሰጣቸዋል። (Holyday is defined as a day of festivity or recreation when no work is done and Feast is defined as a periodic religious observance commemorating an event or honoring a deity, person, or thing. so they have different meanings)።

ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን ስርአት ራሱ የሚከለክላቸው ጥቂት በአላትን ብቻ ነው ቢባልም መጻህፍቱ ግን በአብዛኛው ስራ እንዳይሰራ የሚያዝዙ ናቸው። ለምሳሌ ታምረ ማርያም 33 በአላትን በእመቤታችን ስም ምንም ስራ እንዳይሰራባቸው ይከለክላል። ወደ እውነታው ስንመጣ ግን ከተጻፈው 33 በአላት ውስጥ ምን ያክሉ ይከበራሉ? መጻህፉ የሚያዝዘው እንደ እሁድ ሰንበት እንዲከበር ነው። ይህ አባባል በሁለት መንገድ ከበድ ያለ ነው። አንደኛ መከበር ያለበት ምንም ስራ ሳይሰራ እንደ እሁድ ሰንበት ነው ሲል ሁለተኛ ደግሞ ያላከበሩት ደግሞ መወገዛቸውን ይገልጻል። ወደ እውነታው ስንመጣ ግን እንደ እሁድ ሰንበት በአላቱን እናከብራቸዋልን? ብሎ እንደ እኔ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር በእኔ አስተያየት 5% ኦርቶዶክሳዊ እንደ እሁድ ሰንበት የሚያከብረው ከተገኘ መልካም ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ከአንባቢው ካህን ጀምሮ ውግዘቱን እየያዝን ወደ ቤታችን እየሄድን ነው ማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች በአላት ላይም ቤተ ክርስቲያን የሰራችው ስርአትና ምእመኑ ላይ ያለው የአባበር ስርአት የሚስማማ አይደለም።

ስለዚህ በአላትን ማሰቡ መታሰቢያነቱ ይቅር መባሉ የሚደገፍ አይደለም አከባበሩን ላይ ግን ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልጋል። ስሙንም በአል ከማለት መታሰቢያ ብንለው ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ይመስላል። ቤተ ክርስቲያንም በአላቱን መቀነስ ሳይሆን አከባበሩን የተሻለ ማድረጉ መንፈሳዊነቱን ሳይጎዳ ለምመናንም ሳይከብድ ማክበር ይቻላል። ካህናቱና ምእመናኑ በመታሰቢያ ቀናት እለት ቤተ ክርስቲያን ሄደው እግዚአብሔርን አመስግነው የቅዱሳንን በረከት ተሳትፈው መመለሱ መቸም ባይቀር ጥሩ ነው። ብዙዎቹን በአላት ስራ ሳይሰራ ይከበር የሚለው አስተሳሰብ ግን ትንሽ ከበድ ያለ እና እውነታውን ያላገናዘበ ይሆናል።። በአበይት በአላት ቀን ስራ ባይሰራም ከአከባበራቸው አንጻር የሚያስሄድ ነው።

የምንጠቀምባቸውን መጻህፍት እንቀንስ ጸሎቱ ይቀነስ ስለሚሉት፡ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ስለማይጠቀሟቸው እኛም እንተዋቸው የሚለው አባባል በጣም የተሳሳተ ነው። ምክንያቱ ደግሞ እኛ የሌሉን እነርሱ ያሏቸው እንዳሉ ሁሉ እኛ ያሉን እነርሱ የሌላቸው መጻህፍት መኖራቸውን መቀበል አለብን። እነርሱ መጻህፍቱን በልዩ ልዩ ምክንያት አጥተዋቸዋል ወይንም ትተዋቸዋል። በመሆኑም እነርሱ ስለተዋቸው ብቻ እንተዋቸው ማለት የለብንም። በአንጻሩ የጸሎቱ ጊዜ ከረዘመ ከምእመናን አኗኗር ጋር አለመሄዱ በአሳማኝ ሁኔታ ከተረጋገጠ ሲኖዶስ አይቶ የሚገባውን ማድረግ ይችላል። አሁን ባለው ሁኔታ የየአጥቢያው ካህናት ጊዜ ላለመውሰድ ተጨንቀው አገልግሎቱን እንደ አስፈላጊነቱ ለማጣጣም የሚሞክሩ ናቸው።

## ለትችት የሚዳርጉ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን

ለትችት የሚዳርጉ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን

በመጀመሪያው ጽሑፋችን በኦርቶዶክስ ተሃድሶነት በሁለተኛ ደረጃ የመደብናቸው ሰዎች የሚሉት ሀሳብ አጭርና ግልጽ ነው ቤተ ክርስቲያንን ለትችትና ለነቀፋ የዳረጉ ጉዳዮች በሲኖዶስ አማካኝነት ይስተካከሉ የሚል። አስቀድሞ እንደተናገርነው እነዚህን አካላት አሁን በምንረዳው ሁኔታ ተሃድሶ ማለቱ ቢከብድም ሌላ ስም አላገኘሁላቸውም። ይህ ሐሳብ የአንዳንድ በሳል የማህበረ ቅዱሳን አባላትም ሓሳብ እንደሆነ አውቃለሁ። ቤተ ክርስቲያን በእርግጥ ሊያስተች የሚችል ነገር አላትን ወይንስ ህዝቡን ለማወናበድ የሚቀርብ ክስ ነው? የሚለውን ሐሳብ መነሳቱ አይቀርም።

የሚያስተቹ የሚባሉ ነገሮችን መናፍቃኑ ደጋግመው ጽፈዋቸዋል መጻህፍት አውጥተውባቸዋል ተሳልቀውባቸዋል። ሆኖም ግን መናፍቃኑ የጻፏቸው ጽሑፎች ሁሉ እውነተኞች ናቸው ማለት አይደለም። እነርሱ የእምነት መጉደል ስላለባቸው እነርሱ በእምነታቸው መጉደል ምክንያት የሚጠራጠሩት ሁሉ እንደ ስህተት ቆጥረው ኦርቶዶክስ ውስጥ ይህ ስህተት አለ እያሉ ይጽፋሉ። እነርሱ የሚተቹት የሚታመነውን ጭምር እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ለትችት ይዳርጋሉ የሚባሉ ጉዳዮች የእምነት ነገሮች አለመሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን እንደ እምነት ተቋም በእምነትዋና በቀኖናዋ በሃይማኖታዊ ትምህርቷ ነቀፌታ የለባትም። የምታምነው የአበውን ሃይማኖት መመሪያዋ የአምላክ ቃል የምትኖረውም መንፈሳዊውን ህይወት ነው። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመናት ተቀናቃኝ ስላልነበራትና ቤተ ክርስቲያንን የሚተች ሰው ስላልነበር ሊቃውንቱ ሳያውቁ ወይም በመዘናጋታቸው ምክንያት ብዙ ሊያስተቹ የሚችሉ ነገሮች እና እውነታነት የሌላቸው ጽሑፎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲፈጠሩ ሆነዋል። እነዚህ እውነትነት የሌላቸው ነገሮች

መሰረታዊ ዶግማውንና ቀኖናውን አይንኩት እንጂ በልዩ ልዩ ጉዳዮችና በእምነት ላይ የሚንጸባረቁ ሆነዋል።ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 1950 ዎቹ ድረስ ሲኖዶስ አለመኖሩ ጠንከር ብሎ እነዚህን ጉዳዮች የሚያይ አካል እንዳይኖር አድርጓል።

በዘመናዊ መልእክ ስለቤተ ክርስቲያን እምነትና ስርዓት ግልጽ መጽሓፍትን የጻፉ እንደ አቡነ ጎርጎሪዎስ ካልእ አይነት አባቶች የቤተ ክርስቲያን እምነት የሆነውንና ያልሆነውን ዶግማውንና ቀኖናውን ትውፊቱንና ልማዱን እንዲሁም ባህሉን አብራርተው አስቀምጠውልናል። እኒህ አባት አሁን አስተያየት ለሚሰጡ ወገኖች መነሻ ናቸው። የሃይማኖታችን ገደብና ድንበር ልንረዳው በምንችል ቋንቋ ጽፈውልናልና። በዘመናች ያሉ ዲ/ን ዳንኤል ክብረትን የመሳሰሉ ወንድሞች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ሊያስተቹ የሚችሉ ጽሑፎች እንዴት ሊጻፉ እንደቻሉ በጥናት መልክ ጽሑፎችን አቅርበዋል።

http://wongelforall.files.wordpress.com/2011/11/awalid_metsahift.pdf ገጽ 18

ቤተ ክርስቲያን በዘመንዋ ብዙ መጻህፍትን ጽፋ አሳልፋለች። ምንም እንኳን አብዛኛው መጻህፍቱ ተዘርፈው ወደ አውሮፓ ቢሄዱም ሌሎችም ደግሞ በመቃጠል በእድሜ መርዘም ምክነያት በመበላሸት የጠፉ ቢሆንም በአንድ መረጃ እንደተመለከትሁት በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሁለት መቶ ሺ /200 000/ የብራና መጻህፍት እንደተጻፉ /እንደተባዙ/ ይገመታል። ከእነዚህ መጻህፍት ውስጥ ትልቁን ብዛት የሚይዙት አዋልድ መጻህፍቶቻችን ናቸው። ብዙ መጻህፍት ከውጭ ሃገር ክርስቲያኖች ወደ ግእዝ ቋንቋ የተተረጎሙ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት ተጽፈው የተባዙ ናቸው። ታዲያ እነዚህ መጻህፍት ሲጻፉ የሚገለበጡት በእጅ ጽሁፍ ነው። ኮፒዎችም የሚጻፉት እና የሚባዙት በተለያዩ ግለሰቦች ነው። ሁሉም ጸሓፊያን መንፈሳዊ መሆናቸውና የቤተ ክርስቲያን እውቀት እንደነበራቸው ማረጋገጥ አይቻልም። ይህን ልንል የሚያስችለን ደግሞ አንዳንድ ቀላል ሊባሉ የሚችሉ ስህተቶችን ጭምር ስለምናገኝ ነው።

እንደ ዲያቆን ዳንኤል ጥናት ከሆነ ግን አብዛኛዎቹ ለትችት የሚዳርጉ ነገሮችን መጻህፍቶቻችን ውስጥ ያስገቧቸው መናፍቃን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ መልክ መጉዳት ቢፈልጉም እንደፈለጉት ስላልሆነላቸው በቤተ ክርስቲያን የማይታመኑ ጽሑፎችን በቤተ ክርስቲያን መጻህፍት ውስጥ ማስገባት መረጡ ይላል። ቤተ ክርስቲያን የማታምናቸው እና የማትቀበላቸው ከታሪክ እና ከጊዜ ከቦታ ጋር የማይጣጣሙ ጽሑፎችን በማስቀመጥ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠላ እንድትነቀፍና እንድትተች ምክነያት ሆኑ። የዚህ ደግሞ ዓላማው ኦርቶዶክሳዊው ምእመን በጽሑፎቹ አማካኝነት ሃይማኖቱን እንዲጠላና እንዲንቅ ከእምነትም እንዲያፈነግጥ ነው። አንዳንድ በስህተት ቤተ ክርስቲያን ገበተው ቤተ ክርስቲያንን ያስተቻሉ ከምንላቸው ጽሑፎች ውስጥ የሚከተሉትን ለምሳሌ እንመልከት።

1. ሰዶምና ገሞራን የአቃጠሏት ሐዋርያት ናቸው /በሎጥ ዘመን ነበሩ
2. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም የሙሴ እህት ናት
3. ድንግል ማርያም የይስሓቅን ልጅ ያእቆብን በላባ ቤት ውስጥ እያለ ረዳችው

ሌሎችንም ማቅረብ ቢቻልም ለጊዜው አስፈላጊ አይደለም። አንድ ኦርቶዶክሳዊ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የሚያውቅና የሚቀበል ጸሓፊ ከላይ የተገለጹትን ሊጽፍ አይችልም። የዳንኤል ጥናት እንዳመለከተው መናፍቃን ያስገቧቸው ናቸው አለበለዚያ ደግሞ አላዋቂዎች የጨመሯቸው ናቸው። ሆኖም ሊቃውንቱ እያወቁቸው እና የማያምኑባቸው ሆነው ሳለ ለምን ለማስተካከል አልደፈሩም? ይስተካከሉ የሚልንስ አካል እንደ ጥፋተኛ ማየት ይገባን ይሆን? የጎደለውን መሙላት የተጣመመውን ማቃናትን ቤተ ክርስቲያን ልታስብበት እንደሚገባ ሌሎች ጸሓፊያንም ጽፈዋል። ብዙ ወጣቶች እንደ ምሳሌ የምናየው ዳንኤልም ይህንን አብራርቶታል። **http://www.danielkibret.com/2010/08/blog-post_11.html**

ቅዱስ ሲኖዶስ መጻህፍቱንና ቀኖናዋን እያየ መስተካከል የሚገባውን ማስተካከል ስርዋጽ የገባውን ማስወጣት ያልጠነከረውን ማዳበር ሲኖርበት በአስተዳደሩ መዳከም ምክነያት ይህንን አይቶ ለማስተካከል ዓይን ያለው አይመስልም። ኦርቶዶክሳዊያን ወጣቶች በነገረ ሃይማኖት ከበረታንና መጽሓፍትን ከመረመርን የቤተ ክርስቲያን የሆነውን እና ያልሆነውን መለየት እንችላለን። መናፍቃን መጽሐፍቶቻችንን እየጠቀሱ ለማደናገር ሲሞከሩም አግባብ የሆነ መልስ ለመስጠት አቅሙና እውቀቱ ይኖረናል።

ፕሮቴስታንታንቶች እንደመጠቀሚያነት የሚያደርጓቸው እነዚህን ድክመቶች ነው። ድክመቶቹን የሃይማኖት ድክመት በማስመሰል ኦርቶዶክስ የተሳሳተች ናት በማለት ብዙ ሰው ለማስኮብለል አስችሏቸዋል። ፕሮቴስታንቶች በእየቀኑ ብዙ ሰው የሚያጠምዱት በእነርሱ እምነት ትክክል ስለሆነ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ላይ አንዳንድ ድክመቶች መኖራቸው እና ለምእመኖቻችን እነዚህን ድክመቶች ባለማሳወቃችን ወይንም ባለማሻሻላች ነው። እንዲያውም አንዳንድ ካህናት ሳይቀር ሲጠይቋቸው መልስ መስጠት እስኪያቅታቸውና ሲደናገሩ ይታያሉ። በመሆኑም ድክመቶችን በሚገባ አጥንቶ ማስተካከል ለቤተ ክርስቲያን ጥንካሬና መስፋፋት ለምእመናን መጽናት ለቀጣዩ ትውልድም መረጋጋት የሚፈጥር ነው።

## ሲኖዶስ ያላስተካከለውን እምነት መተቼት ይቻላልን?

መምህራኖቻችን እነዚህን ስህተት የሆኑ ጽሑፎቻችንን እና አንዳንድ ጉዳዮችን እንዴት ሊያዩቸውና ሊያስተምሯቸው ይገባል? መምህራን ትክክለኛውም የእግዚአብሔር ቃል የመናገር ግዴታ ቢኖርባቸውም የቤተ ክርስቲያንን ባህል እና እምነት የሚጻረሩ ጽሑፎችን እና ትምህርቶችን ግን መስጠት የለባቸውም። በአንጻሩ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ እንደሚለው ስህተቶች እንዲስተካከሉ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ማስታወስ ተገቢ ነው። በአደባባይ ግን ይህ ስህተት ነው እያሉ የሚታመነውን መናገሩ ምእመናንን ማደናገር ይሆናል።

ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ ቃል ኪዳን በነገረ ድህነት በሚለው መጽሓፉ በመጨረሻው ምእራፍ በመጽሓፈ ጤፉትና በሌሎች ድርሳናት ላይ ተጽፎ የሚገኝ እና ምእመናን የምናምነውን ግሸንን የተሳለመ ሃጥያቱ ይሰረይለታል የሚለውን አስተምህሮ ትክክል አይደለም ብሎ ጽፏል። ለዚህም ሃጥያት የሚሰረየው በንስሃ እንጂ በቃል ኪዳን አይደለም የሚለውን ለማሳየት ሞክሯል። ጸሐፊው እውነትነት ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የምታምነው እስከሆነ ድረስ ተቃውሞ መጻፉ አግባብ አይደለም። ድርሳናቱ ይህን በተመለከት የጻፉት ስህተትነት ካለው በመጀመሪያ በሲኖዶስ እንዲስተካከል መደረግ አለበት አለበለዚያ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መጻህፍት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲኖሩ ማድረግ ምእመናኑን ለመከፋፈል እና ለትችት መዳረግን ያስከትላል።

## ቤተ ክርስርስቲያን እና የምእመናን ቁጥር

ቤተ ክርስቲያን ብዛት አትፈልግም እግዚአብሔር ብዛት አይፈልግም የሚሉ ሓሳቦች ብዙ ጊዜ ይቀርባሉ። አወ ትክክል ነው ቤተ ክርስቲያን አማኙ ትንሽ ስለሆነ ውሸት አትሆንም እግዚአብሔርም በትንሽ ሰው መስራት ይችላል ከብዛት ይልቅ ጥራትን ይመርጣል። ቁጥሩን ግን በሁለት ወገን እንፈልገዋለን። አንደኛውና የመጀመሪያው ሰዎች ወደ ጥፋት እንዳይሄዱ እንዳይሞቱ ነው። ሰው በሃይማኖት ካልኖረ ወይም በትክክል እግዚአብሔር ሳያውቅ በክህደት እና በኑፋቄ ከኖረ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም። ስለዚህ ዛሬ ወንድማች እህታችን የሆነው ሰው ሃይማኖቱን እንዲተው ወደ ኑፋቄ እንዲገባ ወይንም ሃይማኖት እንዳይኖረው መሆኑ የእግዚአብሔርን መንግስት እንዳያገኝ ስለሚያደርገው ቢቻል ሁሉም በሃይማኖት መኖሩ ቁጥሩ መብዛቱ ጥሩ ነው። ይህ ከግለሰቦች ጥቅም አንጻር ነው። ከቤተ ክርስቲያን እና ከአማኞች አንጻርም የምእመናን ቁጥር ቀላል የማይባል ትርጉም አለው። ዛሬ መካከለኛው ምስራቅ ያሉ ክርስቲያኖች ይህ ሁሉ ግፍ የሚደርስባቸው ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ በእየ አመት በአሉና በእየ እሑዱ የሚታረዱት ቁጥራቸው አናሳ ስለሆኑ ነው። ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ሙስሊሞች ጽንፈኛ ያልሆኑ መንግስታትን ሳይቀር ያንበረክካሉ። ያዝዛሉ። በአውሮፓ እና በደቡብ አሜሪካ  የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተጽኖና ተሰሚነት ቀላል አይደለም ምንም እንኳን በአንዳንድ የአውሮፓ ሐገራት በፕሮቴስታንቶች አማካኝነት ተሰሚነታቸው ቢቀርም። ፕሮቴስታንትም በራሱ ምንም እንኳን እርስ በእርሱ ያለው ክፍፍል ቢኖርም በሰሜን አሜሪካና በአንዳንድ የአውሮፓ ሐገራት ተጽኖ ማሳደር የሚችል ድርጅት ነው።

ቁጥሩ ተጽኖ ለማሳደር አይደለም ዋና አላማው ሆኖም ራስንም ለመከላከል ጭምር እንጂ። በሃገራችን በጅማና ኤሊባቡር አካባቢዎች ክርስቲያኖች ጥቃት የሚደርስባቸው  ቁጥራቸው ስላነሰ እንጂ ህገ መንግስቱ በእነዚያ አካባቢ ስለተለየ አይደለም። ዛሬ በሃገራችን እስልምናውም ይሁን ሉተራዊያኑ ቁጥርን ታርጌት ያደረገ ስራ ይሰራሉ። ሁለቱ በእየንራቸው በምን ያክል ዓመት ሀገሪቱን ወደ ራሳቸው ሃይማኖት ሙሉ ለሙሉ መቀየር እንደሚችሉ ስትራቴጂክ እቅድ ነድፈው ይንቀሳቀሳሉ። የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ ያነበባቸው መዛግብት እንደሚያሳዩት ሙስሊሞች ከ30 እስከ  40 ዓመት ውስጥ ባለው ጊዜ ኢትዮጵያን የእስላም ሐገር እናደርጋለን የሚል እቅድ ሲኖራቸው ሉተራዊያን ደግሞ እስከ 75 ዓመት ብቻ ውስጥ ኢትዮጵያን ፕሮቴስታንት እናደርጋለን ብለው ያስባሉ።  ይህ ባለበት ሁኔታ የተዋህዶ ልጆች ቁጥር ጥቅም የለውም ማለት የሚገባን አይመስለኝም። ነገር ግን እነርሱ ይህን ስላሰቡ ይሳካላቸዋል ማለት አይደለም። ቢሆንም ግን እኛ ከተዘናጋንና ከተለያየን ወደ ፊትም ምእመኖቻችን በተኩላ መነጠቃቸው አይቀርም። ይህን የምናስቀረውና የእኛን እምነትም ማሳደግና መጠበቅ የምንችለው ትክክለኛ ቤተ ክርስቲያን ከስብከቱ ከጾምና ጸሎቱ በተጨማሪ እቅድ እያወጣች መስራት ስትችል ለአንድነት መስራት የሚችሉ ማህበራትና ምእመናንን ማፍራት ስትችል ነው።

**ማስታወሻ:**

በክፍል ሶስት ኦርቶዶክስ ተሃድሶዎች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ካስቀመጥን በኋላ የጸሐፊውን አስተያየት እና እውነታዎች ጀምረን የነበረ ቢሆንም የጸሓፊው አስተያየት የቀረበው በአንደኛው ምድብ ጥያቄያቸው ላይ ብቻ ማለትም ኦርቶዶክስ ተሃድሶዎች ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን አንጻር ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ብቻ ነው። ሌሎቹ ሰፋ ያለ ጽሑፍ የሚያስፈልጋቸው ስለሆነና ጸሓፊው ይህን በተመለከተ የጻፈው ጽሑፍ ስለጠፋበት መውጣት አልቻለም። ወደ ፊት እግዚአብሔር ቢፈቅድ እንደገና የሚጻፍ እና የሚወጣ ይሆናል።

ስበሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመናምልኮ